የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.83
Addis Ababa, this 28th day of June 2024

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፲፮
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

ገፅ…………………………..……. ፫ሺ፯፻፲፬

## Content

Regulation no. 173/2024
Regulation issued to re-establish Addis Ababa city Government Theater housing administration Enterprise

Page ……………………….………..…3714

## ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

ቴአትር ቤቶቹ በገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ህብረተሰቡ ባህልና ታሪኩን እንዲያውቅና እንዲጠብቅ ማድረግ የሚያስችል የኪነ-ጥበብ ውጤት የሆኑ ተውኔቶችንና ቴአትሮችን እንዲሁም ሙዚቃ እና የውዝዋዜ ጥበብ ስራዎችን በመፍጠር፣ በማዘጋጀት ለታዳሚው ተደራሽ እንዲያደርጉ ለማስቻል በአንድ አስተዳደር ስር መደራጀታቸው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አዲስ አበባ ከተማ ከዕለት ወደ ዕለት እያስመዘገበች ላላችው ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን በቴአትር ቤቶች የሚዘጋጁ የኪነ-ጥበብ ሥራዎች በጥራትም ሆነ በብዛት ደረጃቸውን ጠብቀው ትርፋማ ሆነው እንዲወጡ የልማት ድርጅት ሆነው መቋቋማቸው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## REGULATION No. 173/2024
## REGULATION ISSUED TO RE-ESTABLISH ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT THEATER HOUSING ADMINISTRATION ENTERPRISE

**WHEREAS,** it has become necessary to the theaters to be organized under one administration to enable competitiveness in the market by creating and preparing plays and theaters, as well as music and dance art works that enable the society to know and preserve the culture and history;

**WHEREAS,** it has become necessary to speed up the all-round development of Addis Ababa City, it is necessary to establish them as a public enterprise so that the artistic works produced by theaters maintain their standards in terms of quality and quantity and become profitable;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪ እና ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፸፫/፪ሺ፲፮__ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **“ደንብ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ነው፤

፪. **“ቦርድ”** ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የሥልጣን አካል ነው፤

፫. **“ገቢ”** ማለት ቴአትር ቤቶቹ ከኪነ-ጥበብ ውጤቶች፣ ኪራይ፣ ከሽያጭ እና ከልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ ነው፤

፬. **“ቴአትር ቤት”** ማለት እንደአግባብነቱ ሃገር ፍቅር ቴአትር፣ ራስ ቴአትር፣ የአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ እና የህጻናትና ወጣቶች ቴአትር ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የሚደራጅ ሌላ ቴአትር ቤትን ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

**፫. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት (ከዚህ በኋላ “ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ) የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን ይሆናል፤

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub Article (2) of Article 68 and sub Article (1) of Article 93 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This regulation may be cited as “Regulation issued to Re- Establish Addis Ababa City Government Theatre Housing Administration Enterprise Regulation No. 173/2024’’.

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**Regulation**" shall mean the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024;
2. "**Board**" shall mean a body of authority of the Enterprise established in accordance with the Regulation;
3. "**Revenue**" shall mean the theatre’s income from the productions, rentals, sales and miscellaneous services;
4. "**Theatre House**" shall mean the Patriotic Theatre, Ras Theatre, Addis Ababa Theatre and Culture Hall and Children's and Youth Theatre as appropriate and includes other theatres organized as necessary.

## PART TWO
## THE ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ENTERPRISE

**3. Establishment**

1. Addis Ababa City Government Theatre Housing Administration Enterprise (hereafter referred to as "Enterprise") has been established as a Public Enterprise by this regulation;
2. The Enterprise 's Accountability will be to the Administration Authority of Government Public Enterprises of the Addis Ababa City Administration;

፫. ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮__መሠረት ይተዳደራል፡፡
፬. ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው ቴአትር ቤቶች ከዚህ በፊት በሚጠሩበት አጠራር የሀገር ፍቅር ቴአትር፣ ራስ ቴአትር፣ የአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ እና ህፃናትና ወጣቶች ቴአትር በሚል የሚጠሩ ይሆናል፤
፭. በተጨማሪም አዲስ የሚደራጁ ቴአትር ቤቶችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

፬. **<u>የድርጅቱ ዓላማ</u>**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው ውስጥ ቴአትር ቤቶችን ያደራጃል፣ያስፋፋል፤ያስተዳድራል፣ይመራል፤
፪. በከተማው ውስጥ ለህብረተሰቡ አዝናኝና አስተማሪ የሆኑ እንዲሁም ህብረ-ብሔራዊነትና አካታችነትን መሰረት ያደረጉ ትርኢቶችንና ኮንሰርቶችን ያቀርባል፤
፫. ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ በትምህርት ሥርዓቱ የተካተተውን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ቴአትር፣ ሙዚቃ እና የውዝዋዜ ጥበብ በማዘጋጀት ለገበያ ያቀርባል፤ በቀጣይም ተመልካችን መሰረት በማድረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሌሎች ቋንቋዎችን ሊጨምር ይችላል፤
፬. ከተማውን በቴአትርና ሙዚቃ ዘርፍ ተመራጭ መዳረሻ መሆን የሚያስችል የማስተዋወቅ ሥራን ይሰራል፤
፭. አዋጭ በሆነ መንገድና በጥናት አዳዲስ ቴአትር ቤቶችን ያደራጃል፤
፮. የቴአትርና ሙዚቃ እንዲሁም የውዝዋዜ ጥበብ ውጤቶችን ያመርታል፤ በዘርፉ ከተሰማሩ ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤ ለሀገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ገበያ ያቀርባል፤
፯. በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ድጅታል ሚዲያ እና በልዩ ልዩ አማራጮች በሚያቀርባቸው ትርኢቶች፣ ሙዚቃዎችና ኩነቶች ላይ ሀገር በቀልና አለም አቀፍ ተቋማትን ምርት በክፍያ ያስተዋውቃል፤

3. The Enterprise is administered in accordance with the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the Conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024.
4. The theatre houses administered by the Enterprise as pronounced before will be known as the Patriotism Theatre, Ras Theatre, Addis Ababa Theatre and Culture Hall and Children and Youth Theatre;
5. It will also include newly organized theatres.

4. **<u>Objective of the Enterprise</u>**

The Enterprise shall have the following Objectives:-

1. It organizes, expands, administers and directs theatres in the City.
2. Presents performances and concerts in the City that are fun and educational for the community and based on nationalism and inclusiveness;
3. In addition to the Amharic language, which is included in the education system, it will produce theatre, music and dance art in the Afan Oromo language and market it; further, based on the audience, other languages may be added based on research;
4. Promotes the City as a preferred destination for theatre and music;
5. Organizes new theatres in a cost-effective manner and research;
6. Produces theatrical, music and dance productions; it works in cooperation with institutions engaged in the sector; it supplies to the local and international market;
7. Promotes the products of local and international institutions for a fee on various social media, digital media and shows, music and events it offers;

፰. ለቴአትርና ሙዚቃ ኢንድስትሪ እድገት ፕሮጀክትና ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣ ይተገብራል፤

፱. ለቴአትርና ሙዚቃ እንዲሁም ውዝዋዜ ኢንዱስትሪ እድገት ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ይተገብራል፤

፲. የቴአትር ፌስቲቫል እና የሙዚቃ ኮንሰርት ያዘጋጃል፣ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል ላይ ይሳተፋል፤

፲፩. ለቴአትር፣ ለፊልምና ሙዚቃ መስሪያ እና ለልዩ ልዩ ፕሮግራም አገልግሎት የሚውሉ ስስቱዲዮ፣ ቢሮ፣ አዳራሽ፣ ሱቅ፣ ተንቀሳቃሽ መድረክ ወይም ስቴጅ፣ ሳውንድ ሲስተም፣ አውቶብሶች፣ የቴክኖሎጂ ውጤትና ሌሎች የድርጅቱ ንብረቶችን በክፍያ ያከራያል፤

፲፪. ለህጻናት፣ ለወጣቶችና ለጎልማሶች የቴአትርና የሙዚቃ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፲፫. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል፣ ያስከፍላል፣

፲፬. **የሀገር ፍቅር ቴአትር፡-**

ሀ) አገር በቀል የህብረተሰቡ ተጨባጭ ባህሎችንና ትውፊቶችን ሳይበረዙ እና ሳይሸራረፉ በኪነ-ጥበብ አዋዝቶ ማቅረብ፤

ለ) ህብረ ብሔራዊነትን ባማከለ መልኩ የሀገር ፍቅር ስሜት የሚያጎለብቱ የኪነ-ጥበብ ስራዎች በመስራት ውጤታማና ትርፋማ መሆን፤

ሐ) የተለያዩ ሀገርና ዓለም አቀፍ ችግሮች በተጋረጡ ጊዜ ማህበረሰቡን በኪነ-ጥበብ ማነሳሳት፤

መ) ለሀገር ፍቅር ስሜት እና ለበጎ ምግባር የሚተጋ ማህበረሰብ መፍጠር የሚያስችሉ የኪነ-ጥበብ ውጤቶችን ማምረትና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ሠ) የመልካም ገጽታ ግንባታን ለማሳደግ፤ ሀገረሰብ እሴቶችን የሚያስፋፉ የተለያዩ የኪነ-ጥበብ መድረኮች በመጠቀም በህዝቦች መካከል ያለውን የአብሮነት ባህል በማዳበር ከተማዋ ያላትን በጎ-ገጽታ ለዓለም ህብረተሰብ ማስተዋወቅ፤

8. Designs and implements projects and programs for the development of the theatre and music industry;
9. Conducts and implements research for the development of theatre, music and dance industry;
10. It will organizes theatre festivals and music concerts, participates in international and national festivals;
11. Rents studio, office, hall, shop, mobile platform or stage, sound system, buses, technology products and other properties of the organization used for theatre, film and music production and for special programs;
12. Provides or arranges for theatre and music training for children, youth and adults;
13. It trusts and charges for the services it provides.
14. **Patriotic Theatre:**
    a) Presenting the authentic cultures and traditions of the indigenous society through art;
    b) To be effective and profitable by making works of art that promote patriotism in a nationalistic manner;
    c) To inspire the community through art when faced with various national and international problems;
    d) To produce and make accessible artistic works that will create a society that strives for patriotism and virtue;
    e) To increase the construction of a good image; promoting the city's beauty to the world community by developing the culture of solidarity among people by using various art platforms that promote national values;

ረ) በከተማዋ የሚገኙ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የሚያስተሳስሩ ፈጠራዊ ይዘት ያላቸው የኪነ-ጥበብ ምርቶች ማዘጋጃና ማቅረቢያ ማዕከል መሆን፤

ሰ) የኢትዮጵያ ህዝቦችን ታሪክ አጉልተው የሚያሳዩ ታሪካዊ ተውኔቶች እና ቱባ ሙዚቃዎችን በጥናት ላይ በመመስረት እያመረተ ለተመልካች ማቅረብ፡፡

፲፭. **የራስ ቴአትር፡-**

ሀ) የኪነ-ጥበብ ተሰጥዖ ያላቸው አማተር እና አዳዲስ የሙያ ምሩቃንን በመለየት በሙያዊ ዲሲፕሊን ብቁ የማድረግ መዳረሻ መሆን እና ወደ ኢንዱስትሪው የሚቀላቀሉበትን ሁኔታ መፍጠር፤

ለ) በጥናትና ምርምር የታገዙ፣ ደረጃቸው ላቅ ያሉና የበለፀጉ አዳዲስ ኪነ-ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ትርፋማ መሆን፤

ሐ) የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ የተለያዩ የኪነ-ጥበብ መድረኮች በማዘጋጀት በህዝቦች መካከል ያለውን የአብሮነት ባህልን ለማዳበር፤

መ) ሃገርኛ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አቅም ማጎልበቻ ማዕከል መሆን፤

ሠ) የተለያዩ ሀገራዊ ኦርኬስትራዎች እንዲፈጠሩ፣እንዲበራከቱና እንዲስፋፉ በመስራት የተሞክሮና የልህቀት ማበልፀጊያ ማዕከል መሆን፤

ረ) የኪነ-ጥበብ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ በስነ-ምግባር የታነፁና በክህሎት የዳበሩ ተተኪ ሙያተኞችን ማፍራት የሚያስችሉ የአማተርኪነ-ጥበባዊ አውደ ትርኢቶችን ማዘጋጀት፤

ሰ) አእምሮው የበለፀገ፣ ተመራማሪ፣ ችግር ፈቺና መፍትሄ ጠቋሚ፣ ሃገር ወዳድ ማህበረሰብ ለመፍጠር እያዝናኑ ትምህርት የሚሰጡና የሚያመራምሩ፣ ከዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር የሚራመዱ የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን ለህብረተሰቡ ማቅረብ፤ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ቴክኒክና ሙያዎችና መሰል ሙያዊ ተቋማት ጋር በጥምረት በመስራት የኪነ-ጥበብ ማጎልበቻ ማዕከል መሆን፤

f) To be a centre for the preparation and presentation of art products with creative content that bind the ethnicities and peoples of the City;

g) Producing historical plays and different music that highlight the history of the people of Ethiopia based on research and presenting it to the audience.

15. **Ras Theatre:**

a) To identify artistically talented amateurs and new professional graduates and become a destination for qualification in professional disciplines and create conditions for them to join the industry;

b) To be profitable by preparing and presenting new artistic creations, which are advanced and rich, supported by research;

c) To develop the culture of solidarity among people by preparing various art platforms that strengthen people-to-people relations;

d) To be a capacity building centre for national musical instruments to compete internationally;

e) To be a centre of experience and excellence by working for the creation, proliferation and expansion of various national orchestras;

f) To prepare amateur art fairs that can produce ethically trained and skilled successors who will play a significant role in the development of art;

g) Providing art works to the society that educate and research while entertaining to create a rich minded, researching, problem-solving and solution-seeking, patriotic society; to be an art development centre by working in collaboration with universities, colleges, technical and vocational and similar professional institutions.

፲፮. <u>የቴአትርና ባህል አዳራሽ</u>

ሀ) ዓለም አቀፋዊ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን መስራት፤ ከከተማዋ ጋር ለሚደረጉ የዲፕሎማሲዊ ትስስር የባህል ልውውጥ አንዱ አካል በመሆን፤ የከተማውን ማህበረሰብ የሚገልጽ እና የሚያንጽ የኪነ-ጥበብ ሥራዎች የሚቀርቡበት መዳረሻ ተቋም እና ትርፋማ መሆን፤

ለ) የከተማውን ሁለንተዊ ገጽታ የሚያሳዩ የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን ማቅረብ፤

ሐ) በውጭ ቋንቋዎች ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶችን ማቅረብ፤

መ) ዘመናዊ የኪነ-ጥበብ ትርኢቶች መዳረሻ ማዕከል መሆን፤

፲፯. **የህፃናትና ወጣቶች ቴአትር**

ሀ) የከተማዋ ህፃናት ታዳጊና ወጣቶች በስነ ልቦና፣ በስነ ምግባር እና በሞራል እንዲሁም በአካታችነት መርህ ታንፀው የሚያድጉበትን የኪነ-ጥበብ ስራዎች አዘጋጅቶ ማቅረብና ወደ ሙያው ለሚመጡ ታዳጊ ባለሙያዎች ተከታታይ ስልጠና በመስጠት ብቁና ተተኪ ባለሙያዎችን ማፍራት፤

ለ) ሀገራችን የፈረመቻቸውን አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የህፃናት የመብት ስምምነትና ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች መፍጠሪያ፤ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ማዕከል መሆን፤

ሐ) በከተማው ላሉ ህፃናት ታዳጊና ወጣቶች ተከታታይ ስልጠና በመስጠት ተተኪ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ማፍራት፤

መ) በከተማችን ውስጥ የሚሰሩ የህፃናት ታዳጊና ወጣቶች የኪነ ጥበብ ሥራዎችን በሙያ መደገፍ፤

ሠ) በህፃናት በታዳጊና በወጣቶች የኪነ-ጥበብ እንቅስቃሴዎችና ውጤቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

16. **Theatre and Culture Hall:**

a) Creating international works of art; being part of the cultural exchange for diplomatic ties with the City; to be a destination institution for the presentation of works of art that define and build the City's Community and be profitable;

b) To present works of art that depict the universal aspect of the City;

c) Presenting artistic events to the diplomatic community in foreign languages;

d) To be a destination centre for contemporary art exhibitions.

17. **Children and Youth Theatre:**

a) Prepare and present works of art in which the City's Children and Young People can develop psychologically, ethically and morally, and grow up with the principle of inclusiveness, and by providing continuous training to young professionals who come to the profession, to produce qualified and successor professionals;

b) Creation of artistic works based on the international and continental children's rights agreements and provisions that our country has adopted; to be a preparation and delivery centre;

c) To provide continuous training for Children and Youth in the City to produce replacement artists;

d) Children and Young People working in our City by supporting artistic works;

e) To serve as a research and research centre for the artistic activities and results of Children, Teenagers and Young People;

ረ) ህፃናትና ታዳጊዎች እየተዝናኑ የንባብ ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበትን አውድ በመፍጠር የእውቀትና የመዝናኛ ተመራጭ የኪነ-ጥበብ ተቋም መሆን፤

ሰ) ታዳጊዎችና ወጣቶች ማንነታቸውን፣ የአገራቸውን ታሪክ፣ ባህላቸውን፣ እሴታቸውንና የመሳሰሉትን የሚያውቁበት የኪነ-ጥበብ ተቋም ሆኖ ማገልገል፤

ሸ) ልዩ ድጋፍ የሚሹ ህፃናትንና ታዳጊዎችን በልዩነት እያዝናና ማስተማር የሚችል ተቋም መሆን፤

ቀ) በሰርከስ ትርኢት ህጻናት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

በ) በኪነ-ጥበብ ስልጠና ዘርፍ የልህቀት ማዕከል እንዲሆን ማድረግ፡፡

፲፰. ከቴአትር እና ሙዚቃ ሥራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ይሰራል፡፡

፭. **<u>ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ</u>**

፩. የተለያዩ ሀገርና ዓለም አቀፍ ችግሮች በተጋረጡ ጊዜ ማህበረሰቡን በኪነ-ጥበብ ማነሳሳት፤

፪. ለሀገር ፍቅር ስሜት እና ለበጎ ምግባር የሚተጋ ማህበረሰብ መፍጠር የሚያስችሉ የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን መፍጠር ፣ ማዘጋጀት እና በማቅረብ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፫. የመልካም ገጽታ ግንባታን ለማሳደግ፤ ሀገረሰብ እሴቶችን የሚያስፋፉ የተለያዩ የኪነ-ጥበብ መድረኮች በመጠቀም በህዝቦች መካከል ያለውን የአብሮነት ባህል በማዳበር ከተማዋ ያላትን በጐ-ገጽታ ለዓለም ህብረተሰብ ማስተዋወቅ፤

፬. በከተማው በተለያዩ የበጎ ፈቃድ ተግባራት ላይ መሳተፍ፡፡

f) To be the preferred art institution for knowledge and entertainment by creating a context where Children and Teenagers can develop their reading skills while having fun;

g) Serving as an art institution where Teenagers and Young People can learn about their identity, their country's history, culture, values, other related aspect.;

h) To be an institution capable of entertaining and educating Children and Teenagers who need special support;

i) To qualify Children in circus performances;

j) To make it a centre of excellence in the field of arts training;

18. It also does other work related to theatre and music productions.

5. **<u>The Public Service Obligation that the Enterprise is Expected to Provide</u>**

1. To inspire the community through art when faced with various national and international problems;
2. To create, prepare and present works of art that enable the creation of a society dedicated to patriotism and virtue, making them accessible;
3. To promote good image building; promoting the city's beauty to the world community by developing the culture of solidarity among people by using various art platforms that promote national values;
4. Participating in various voluntary activities in the city.

## ፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊየን ፰፻፭ ሚሊየን ፯፻፵፭ሺ ፮፻፸፪ብር (ሁለት ቢሊዮን ስምንት መቶ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ቢሊየን ፰፻፭ ሚሊየን ፯፻፵፭ሺ ፮፻፸፪ ብር (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር) በአይነት እንዲሁም ብር ፩፻ ሚሊየን ብር (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ተከፍሏል፡፡

## ፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፰. ዋና መስሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ክልል ውስጥ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፱. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

## ፲. የድርጅቱ አደረጃጀት

ድርጅቱ:-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

፫. ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

## ፲፩.ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

## ፲፪. የተሻረ ሕግ

የአዲስ አበባ ከተማ የቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፶፪/፪ሺ፲፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

## 6. Capital

The authorized capital for the Enterprise is Birr 2,805,745,672.00 (two billion eight hundred five million seven hundred forty five thousand six hundred and seventy two) Birr, of which Birr 1,805,745,672.00 (One billion eight hundred five million seven hundred forty five thousand six hundred seventy two) Birr in kind and Birr 100,000,000 (One hundred million) Birr was paid in cash.

## 7. Liability

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

## 8. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the country as may be necessary.

## 9. Supervisory Authority

Addis Ababa City Administration Public Enterprise Administration Authority shall be the Enterprise's Supervisory Authority.

## 10. Organizational Structure

The enterprise shall have:

1. Management Board of the Enterprise;
2. A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers as necessary and;
3. The necessary staff.

## 11. Duration of the Organization

The Enterprise is established for an indefinite period duration.

## 12. Repealed Law

The Establishment of Addis Ababa City Theatre Housing Administration Organization Regulation No. 152/2023 is repealed by this regulation.

፲፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ.፲፮ ዓ.ም. ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ.፲፮ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**13. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of this 28th day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**